Arlington Public Schools

# የቨርጂኒያ ቅድመ ትምህርት ቤት ተነሳሽነት (VPI) ለማመልከት የሚያስፈልጉ ሰነዶች - 2025-2026

## <u>የቨርጂኒያ ቅድመ ትምህርት ቤት ተነሳሽነት (VPI) ማመልከቻዎችን የማስረከብ ሂደት</u>

1. **አስፈላጊ የስልክ ማጣሪያ፡-** ለቪፒአይ (VPI) ብቁነታቸውን ለማወቅ ቤተሰቦች በ703-228-8632 (እንግሊዝኛ) ወይም 703-228-8000፣ አማራጭ 1 (ስፓኒሽ) መደወል አለባቸው።
2. **ብቁ ለሆኑ ቤተሰቦች በአካል ቀጠሮ፡-** ብቁ የሆኑ ቤተሰቦች ሰነዶቻቸውን ለማቅረብ እና የቪፒአይ (VPI) ማመልከቻን ከAPS ሰራተኞች ጋር ለመሙላት ቀጠሮ መያዝ አለባቸው።
3. **ማመልከቻ ማስገባት**፡- ማመልከቻዎች በአካል በተገኙበት የቀጠሮው ጊዜ ብቻ ሊቀርቡ ይችላሉ።

## <u>አስፈላጊ ሰነዶች</u>

ለቪፒአይ (VPI) ፕሮግራም ግምት ውስጥ ለመግባት፣ በአካል በሚገኙበት የቀጠሮ ጊዜ ቀጥለው የተዘረዘሩት አስፈላጊ ሰነዶችን ያቅርቡ።

1. ***የልጁ ዕድሜ እና ህጋዊ ስም ማረጋገጫ፡-*** ለ2025-2026 የVPI ቅድመ ትምህርት ፕሮግራም ብቁ ለመሆን ህጻኑ በሴፕቴምበር 30፣ 2025 ወይም ከዛ በፊት 4 አመት መሙላት ይኖርበታል፡፡
    - ***ዋናው የልደት የምስክር ወረቀት***፡- ዋናው የልደት የምስክር ወረቀት በእንግሊዝኛ ካልሆነ፣ ኦፋሻል (የተረጋገጠ) ትርጉሙ ማያያዝ ያስፈልጋል፡፡

2. ***የነዋሪነት ማረጋገጫ***፡- ወላጆች/ህጋዊ አሳዳጊዎች በአርሊንግተን ካውንቲ ከልጃቸው ጋር እንደሚኖሩ ማረጋገጫ ማሳየት ይጠበቅባቸዋል፡፡

<u>***የንብረት ባለቤትነት ወይም ተከራይነት***</u>

ልጁ ወላጆቹ ወይም ህጋዊ አሳዳጊዎቹ በባለቤትነት በያዙት ወይም በተከራዩት ቤት ውስጥ የሚኖር ከሆነ፤ **ሶስት (3) ሰነዶች መቅረብ አለባቸው፡፡**

**ከሚከተሉት ሰነዶች ውስጥ <u>አንዱ</u> (1) መቅረብ አለበት፡-**

- **ስመርስት**፡- *የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች የቤቱ ባለቤት መሆናቸውንና በአርሊንግተን እንደሚኖሩ የሚያሳይ፣*
- **የአሁኑ የሊዝ ስምምነት**፡- በወላጆች/አሳዳጊዎች ስም በአከራይና ተከራይ ወይም ተከራይ እና ባለንብረት የተፈረመ፣
- **የቤት ግዢ ሰነድ**፡- ስመርስቱ ካልተመዘገበ እና ከአዲስ የቤት ግዢ የተገኘ ሰነድ፣

**እና**

***የወላጆች/ህጋዊ አሳዳጊዎች ስምና አድራሻ የሚያሳዩ ከሚከተሉት <u>ሁለቱ</u> (2) ደጋፊ ሰነዶች መቅረብ ይኖርባቸዋል፡-***

- *የአሁኑ የፌዴራል፣ የስቴት ወይም የንብረት ግብር ተመላሾች፣ የአሁን የደመወዝ ክፍያ ገላጭ፣ የአሁኑ የተሽከርካሪ ምዝገባ ካርድ፣ የአሁን የፍጆታ ክፍያዎች፣ የአሁኑ አድራሻ ያለው የሚያገለግል የቨርጂኒያ መንጃ ፍቃድ ወይም በመንግስት የተሰጠ መታወቅያ፣ከአርሊንግተን ካውንቲ የድጋፍ ገንዘብ ሰነድ፣ የአሁኑ የባንክ መገለጫ፣ በአድራሻዎት የተመዘገበ ወቅታዊ የቤት ባለቤትነት ወይም የተከራይ ኢንሹራንስ ፖሊሲ፣ የመራጮች ምዝገባ ካርድ፣የአሁኑ የገቢ ግብር ቅጽ 1099 ወይም ተቀናሽ W2*

<u>***በጋራ መኖሪያ ቤት (የሌላ ሰው መኖሪያ ቤት) ከልጃቸው ጋር ለሚኖሩ ቤተሰቦች***</u>

ወላጆች/ህጋዊ አሳዳጊዎች በሌላ ሰው መኖርያ ቤት ከልጃቸው ጋር በጋራ የሚኖሩ ከሆኑ፤ **አምስት (5) ሰነዶች መቅረብ አለባችው፡፡**

**የሚከተሉት ሶስት (3) ሰነዶች መቅረብ አለባቸው፡-**

- **<u>ቅጽ A</u>፡-** የወላጅ/ህጋዊ አሳዳጊ/የአዋቂ ተማሪ የነዋሪነት ማረጋገጫ ጽሑፍ፣
- **<u>ቅጽ B</u>፡-** የአርሊንግተን ነዋሪ ማረጋገጫ መግለጫ ጽሑፍ፣
- **ስመርስት <u>ወይም</u> የአሁኑ የሊዝ ስምምነት <u>ወይም</u> የቤት ግዢ ሰነድ** (ስመርስቱ ካልተመዘገበ እና ከአዲስ የቤት ግዢ የተገኘ ሰነድ)

**እና**

**የወላጆች/ህጋዊ አሳዳጊዎች ስምና አድራሻ የሚያሳዩ ከሚከተሉት <u>ሁለቱ</u> (2) ደጋፊ ሰነዶች መቅረብ ይኖርባቸዋል፡-**

- *የአሁኑ የፌዴራል፣ የስቴት ወይም የንብረት ግብር ተመላሾች፣ የአሁን የደመወዝ ክፍያ ተመላሽ፣ የአሁኑ የተሽከርካሪ ምዝገባ ካርድ፣ የአሁን የፍጆታ ክፍያዎች፣ የአሁኑ አድራሻ ያለው የሚያገለግል የቨርጂኒያ መንጃ ፍቃድ ወይም በመንግስት የተሰጠ መታወቅያ፣ከአርሊንግተን ካውንቲ የድጋፍ ገንዘብ ሰነድ፣ የአሁኑ የባንክ መገለጫ፣ በአድራሻዎት የተመዘገበ ወቅታዊ የቤት ባለቤትነት ወይም የተከራይ ኢንሹራንስ ፖሊሲ፣ የመራጮች ምዝገባ ካርድ፣የአሁኑ የገቢ ግብር ቅጽ 1099 ወይም ተቀናሽ W2፡፡*

የመኖሪያ ቅጾች A እና B በዚህ በAPS ድህረገጽ https://www.apsva.us/registration/required-documents/ ላይ ይገኛሉ፡፡

3. ***የወላጅ ማንነት እና ከተማሪ ጋር ያላቸው ግንኙነት ማረጋገጫ*** ፡- ወላጆች/ህጋዊ አሳዳጊዎች ትክክለኛ ፎቶ ያለበት በመንግስት የተሰጠ መታወቂያ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
    - *ማንኛውም በመንግስት የተሰጠ ፎቶ ያለበት መታወቂያ ወይም የመንጃ ፍቃድ ወይም ፓስፖርት*
4. ***የገቢ ማረጋገጫ***፡-የVPI ብቁነትዎን ለመወሰን የቤተሰብ ገቢ መረጃ መሰብሰብ አለብን፡፡
    ከሚከተሉት ውስጥ <u>አንዱ (1)</u> ለእያንዳንዱ ከልጁ ጋር ለሚኖር ወላጅ ወይም ህጋዊ አሳዳጊ መቅረብ አለበት፡
    - **የ2023 የገቢ ግብር ተመላሽ (1040)-** የደመወዝ እና የግብር ቅጾችን ጨምሮ የ2023 የገቢዎትን ግብር ተመላሽ ለማስመዝገብ የተጠቀሙባቸውን እንደ W-2 ወይም 1099 ያሉ ቅጾች፣
    - **3 የቅርብ ጊዜ የደሞዝ ክፍያ ተመላሾች**፡- የወላጅ ስምና በዛች የክፍያ ግዜ ያገኙትን ከቀረጥ በፊት ጠቅላላ ደሞዝ የሚዘርዝር፣
    - **የቅጥር ደብዳቤ**፡- የሰራተኛው ስም፣ አጠቃላይ የክፍያ መጠን፣ አጠቃላይ የስራ ሰዓት ቁጥር ወይም የደመወዝ አከፋፈል ብዛትና የሚዘረዝር በኩባንያው ደብዳቤ ሄደር ላይ የተጻፈ ከአሁኑ አሰሪዎ የቅጥር ማረጋገጫ ደብዳቤ፤ አሠሪው መፈረም እና ቀን መጻፍ ይኖርበታል፡፡
    - ***ለተቸገሩ ቤተሰቦች ጊዜያዊ እርዳታ (TANF)፣ ተጨማሪ የደህንነት ገቢ (SSI)፣ ሜዲኬይድ ወይም ተጨማሪ የገንቢ ምግቦችን እርዳታ ፕሮግራም (SNAP)***፡- የልጁ ወላጆች የማይሰሩ ከሆኑ ለቪፒአይ (VPI) የገቢ ብቁነታቸውን ለማረጋገጥ፣ ኦፍፊሻል (ከመስርያ ቤቶች የሚላኩ) ሰነዶች (ለምሳሌ፣ የሽልማት ደብዳቤ፣ የድርጊት ማስታወቂያ፣ የSNAP ካርድ) ግልጋሎት ላይ ይውላሉ፡፡
    - **የልዩ ትምህርት የብቃት ደብዳቤ ወይም የአሁኑ የተናጠል የትምህርት ፕሮግራም (IEP)**፣ ልጁ IEP ካለው።

***ሁሉም የገቢ ምንጮች መካተት አለባቸው።** ተጨማሪ የገቢ ምንጮች፥የቅጥር ገቢዎች፣ የሥራ አጥነት እና የሰራተኛ ካሳ ክፍያዎች፣ የወታደራዊ ጡረተኛ ጥቅማ ጥቅም ክፍያዎች፣ ከአደጋ የተረፉ ጥቅማ ጥቅም ክፍያዎች፣የጡረታ አበል ወይም የጡረታ ክፍያዎች፣ወለድና የትርፍ ክፍፍሎች፣የቤት ኪራይ ወይም የባለቤትነት ክፍያዎች፣ከንብረቶችና ድርጅቶች የሚገኙ ገቢዎች፣ ለትምህርት እርዳታ የሚገኝ ገቢ፣ተቆራጭ/የትዳር ጓደኛ ድጋፍ እና የልጅ ድጋፍ/ተቆራጭና ከቤተሰብ ውጭ የሚገኝ የገንዘብ ድጋፍን ያካትታል።

ያለ አስፈላጊው ደጋፊ ሰነዶች የገቡ የቪፒአይ (VPI) ማመልከቻዎች ወደ ሂደት የሚገቡ አይሆኑም፡፡ የቪፒአይ (VPI) ቅድመ ትምህርት ቤት መቀበል የሚወሰነው በቨርጂኒያ ቅድመ ትምህርት ቤት ተነሳሽነት ፕሮግራም የብቃት መስፈርቶች ነው፡፡ ስለ ቪፒአይ (VPI) ፕሮግራም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን ድህረገጽ https://www.apsva.us/early-childhood-prek/virginia-preschool-initiative-vpi/ ይጎብኙ።